# በቤተ መንግስቱ፤

## ሰማይ ጠቀስ መንታ ህንጻዎች ሊሰሩ ነው

(ዳዊት ከበደ ወየሳ - ዘና ዜና)

ዘና ዜና ማለት፤ አዲስ የተፈጠረ... አንባቢዎች ዘና የሚሉበት፤ ነገሮችን ትኩረት ሰጥተው የማይጨናነቁበት፤ የደራሲው ፈጠራ የታከለበት በአጭሩ እራስዎን ፈታ ዘና የሚያደርግ የአራዳ ልጆች ወግ ወይም ወሬ አልያም ጨዋታ ማለት ነው።



አሁን ቤተ መንግስቱ ያለበት ቦታ ባለ 44 ፎቅ፤ መንታ ህንጻ ሊሰራ መሆኑ ታወቀ። ምናልባት የ4 ኪሎውን የምኒልክ ቤተ መንግስት ማፍረስ፤ በህዝቡ ዘንድ ቅሬታ ሊያስከትል ስለሚችል፤ የፕሮጀክቱ ዜና በኢትዮጵያ ሚዲያ እንዳይገለጽ መደረጉን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አረጋግጧል።

እስካሁን በአዲስ አበባ የሚሰሩት ህንጻዎች በቁመት፤ ከቤተ መንግስቱ ከፍታ በታች ሆነው እንዲሰሩ ህጉ ያስገድድ ነበር። ይህ ህግ ደግሞ ከቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመን ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ ነው። ዋናውም ምክንያት ከቤተ መንግስቱ ከፍታ በላይ ህንጻ ከተሰራ፤ ከዚያ ላይ ሆኖ፤ እንደላውንቸር አይነት የጦር መሳሪያ ወደ ቤተ መንግስቱ በመተኮስ አደጋ እንዳይደርስ ለመቆጣጠር ሲባል ነው። በዚህም ምክንያት ለበርካታ አመታት በአዲስ አበባ ውስጥ ቤተ መንግስቱን በከፍታ የሚበልጥ ህንጻ ሳይሰራ ቆይቷል።

የምኒልክ ቤተ መንግስት በ1879 ዓ.ም. ሲገነባ፤ በከፍታ ቦታ ላይ በመገንባቱ ምክንያት አሁንም ድረስ ከየትኛውም አቅጣጫ ከፍ ብሎ የሚታይ ግቢ ሆኖ ቆይቷል። በቀዳማዊ ኃይለስላሴም ሆነ በደርግ ዘመነ መንግስት በግቢው ውስጥ የጎላ የህንጻ ስራ እንቅስቃሴ አልተደረገም። በርግጥ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመን የንጉሡ ቤተ መንግስት ወደ ታችኛው የኢዮቤልዩ ቤተ መንግስት በመሸጋገሩ ምክንያት የላይኛው ቤተ መንግስት መለስተኛ የጦር ካምፕ ሆኖ ነበር የቆየው።




ሼኽ መሃመድ የሚድሮክ ባለቤት እና አቶ አብነት ገብረመስቀል የሚድሮክ ስራ አስኪያጅ

በደርግ ዘመን ደግሞ፤ ኮሎኔል መንግስቱም ሆኑ ሌሎች ባልደረቦች በሚያምረው የኢዮቤልዩ ቤተ መንግስት ውስጥ መቀመጥን ስላልፈለጉ በአራት ኪሎው የምኒልክ ቤተ መንግስት ውስጥ ተገድበው ነበር የቆዩት። ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ወዲህ በግቢው ውስጥ መጠነኛ የቤት ስራ እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር። በተለይም የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ መኖሪያ ቤት እና እንግዳ የሚቀበሉበት እልፍኝ በተሻለ ሁኔታ ተሰርቶ እንደነበር የሚታወስ ነው። አሁን ግን እነዚህ ሁሉ ቤቶች እና መኖሪያ ቤቶች ተደምስሰው በአይነቱ ሰማይ ጠቀስ የሆነ መንታ ፎቅ ሊሰራ ነው የታሰበው።

ይህ መንታ ሰማይ ጠቀስ ህንጻ እያንዳንዱ 44 ፎቅ ያለው ሲሆን፤ ጨረታውን ያሸነፈው የሼኽ አላሙዲን ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ነው። ሆኖም በህወሃት ስር፤ የኤፈርት ንብረት የሆነው መስፍን ኢንጂነሪንግ "ጨረታው ለኔ ሊሰጠኝ ይገባል" የሚል አቤቱታ በማቅረቡ ምክንያት ጉዳዩ ለጊዜው እንዲዘገይ ተደርጓል። ሆኖም በነአቶ በረከት ስምኦን በኩል እንደመደራደሪያ የቀረበው ሃሳብ፤ "ቢያንስ ለህንጻው ማሰሪያ የሚሆነው ሲሚንቶ፤ ከህወሃቱ የመሰቦ ፋብሪካ ይወሰድ።" የሚል አስታራቂ ሃሳብ ቢቀርብም፤ "ሚድሮክ በቅርቡ ያስመረቀው ደርባ ሲሚንቶ ፋብሪካ በቂ የሲሚንቶ ውጤት ስላለው፤ የመሰቦን ሲሚንቶ አንቀበልም።" የሚል ምላሽ ነው የሰጠው። በሌላ በኩል ለህንጻዎች ብረት በማቅረብ የሚታወቀው የመከላከያ ሚኒስትር በመሆኑ፤ በጉዳዩ ላይ ሜጀር ጄነራል ሳሞራ የኑስ ጣልቃ በመግባት፤ "ለህንጻው የሚሆነው ብረት በሙሉ ከመከላከያ እንዲወሰድ" የሚል ትዕዛዝ በመስጠታቸው ለስራው መጓተት እንደዋነኛ ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል።

የሚድሮክ መስሪያ ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ የሆኑትን አቶ አብነት ገብረመስቀልን በስልክ አግኝተን እንዳናገርናቸው ከሆነ፤ ፕሮጀክቱን ሚድሮክ ማሸነፉ ትክክል ነው። ሆኖም ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን ለመናገር ፈቃደኛ አይደለሁም።" ብለዋል።

አሁን ያለው ውዝግብ ጋብ ካለ፤ ባለ መንታው ህንጻ እያንዳንዱ 44 ፎቆች ሲኖሩት፤ የምድር ቤቱን ጨምሮ አራቱ ደርቦች በውስጣቸው ትላልቅ ሱቆች እና መዝናኛ ስፍራ ይኖራቸዋል። በዚህ መዝናኛ ስፍራ ከውሃ ዋና ጀምሮ ሳውና፣ ጂምናዝየም፣ ምግብ እና ካፌ ቤቶች ይኖራሉ። ከመንታዎቹ አንደኛው ህንጻ ሙሉ ለሙሉ ለመንግስት ስራ የሚያገለግል ሲሆን፤ ሁለተኛው መንታ ህንጻ ደግሞ ለልዩ ልዩ ስራዎች ወደ አዲስ አበባ ለሚመጡ የውጭ እንግዶች የሚከራይ፤ የተለያዩ አገራት ርዕሳነ ብሄራት የሚያርፉበት ይሆናል።

በግራ በኩል ያለው ህንጻ ሙሉ ለሙሉ የመንግስት

ባለስልጣናት ለስራም ሆነ ለእረፍት፤ ለስብሰባ እና ለኑሮ የሚቆዩበት ቦታ ነው የሚሆነው። በተለይም በህንጻው የመጨረሻ አናት ላይ የጠቅላይ ሚንስትሩ እና የካቢኔያቸው ቢሮ ይገነባል። ከዚህ 44ኛ ፎቅ ላይ በመሆን አዲስ አበባን በሁሉም አቅጣጫ ማየት የሚቻል ሲሆን፤ ምናልባት ወታደራዊ ጥቃት ቢሰነዝር በሚል የመከላከያ ሚንስትር በዚሁ 44ኛ ፎቅ ላይ የአየር መቃወሚያ አነስተኛ፤ ተሰፈንጣሪ ሚሳየሎችን ለመትከል የእስራኤልን ዘመናዊ መሳሪያዎች በመግጠም ከሚታወቀው אפריל የተባለ ድርጅት ጋር፤ መንግስት የስምምነት ውል ማድረጉ ተያይዞ ተገልጿል።



ጠቅላይ ሚንስትሩን ጨምሮ፤ ሌሎች የመንግስት ባለስልጣናት ወደ ቦሌ ኤርፖርት ወይም ወደሌሎች ቦታዎች ሲሄዱ እንደከዚህ ቀደሙ መንገድ አዘግተው በአዲስ አበባ ጎዳና ላይ አይሄዱም። ይልቁንም ከነዚህ ሁለት ህንጻዎች አናት ላይ ሆነው ዝግጁ ሆነው የሚጠብቁ በደህንነት መስሪያ ቤቱ ስር የሚታዘዙ ሄሊኮፕተሮች ይኖራሉ። ወደፊት በቤተ መንግስቱ የምስራቅ አቅጣጫ ላይ በሚገኘው ሰፊ ሜዳ ላይ አነስተኛ አውሮፕላኖችን ለማሳረፍ የሚቻልበት ሁኔታም ገחאየተባለው የእስራኤል ሲቪል አቪየሽን መስሪያ ቤት ጥናቱን አጠናቋል።

ከምንም በላይ ግን ህንጻውን አስደናቂ የሚያደርገው፤ በህንጻው በሁሉም አቅጣጫ የሚገጠሙት የኬብል ትራንስፖርት መስጫ መኪኖች ናቸው። በጠንካራ መሰረት ላይ በሚገነባው በዚህ ህንጻ ላይ በሁሉም አቅጣጫ፤



ከአዲስ አበባ ውጪ የሚወስዱ በኬብል ላይ የሚዘውሩ መኪኖች ይኖራሉ። እነዚህ መኪኖች እያንዳንዳቸው አስራ ሁለት ሰዎችን የሚጭኑ ሲሆን፤ በሰአት 120 ኪሎ ሜትር ወይም 50 ማይል ይጓዛሉ። በዚህ ፍጥነት በመጓዝ ወደ ቢሾፍቱ፣ ሱሉልታ፣ ቡራዩ፣ ሆለታ፣ ቃሊቲ፣ ሰበታ መሄድ ይችላሉ። ሆኖም እነዚህ አዲስ አበባን የከበቡት ከተሞች በሙሉ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው፤ ጨፌ ኦሮሚያ በፕሮጀክቱ ላይ ተነጋግሮ እስከላጸደቀው ድረስ የኬብል መኪኖቹ ስራ በፍጥነት ተግባራዊ ላይሆን እንደሚችል ለፕሮጀክቱ ቅርበት ያላቸው ሚስተር ሉፍ ገልጸውልናል።

ባለፈው ሳምንት ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፤ አዲስ አበባ ላይ ለጋዜጠኞች መግለጫ በሰጡበት ወቅት የነዚህ ባለ አርባራት ፎቅ መንታ ህንጻዎች ጉዳይ በጥያቄ መልክ ተነስቶባቸው፤ የተድበሰበሰ መልስ ነበር የሰጡት። “በመጀመሪያ ደረጃ አርባራት ፎቅ መሰራቱን ከአርባአራቱ ታቦት ጋር እያዛመዱ የሚናገሩ አክራሪ ክርስቲያኖች አሉ። እነዚህ ሃይሎች በተለይ ከማህበረ ቅዱሳን ጋር ያላቸው ግንኙነት መጣራት አለበት። መንታ ህንጻ ግራና ቀኝ በመሰራታቸው፤ የቀድሞ የቅንጅትን አርማ ይመስላል፤ የሚል አፍራሽ እና ኋላቀር አስተሳሰብም ሰምተናል። የነዚህ ህንጻዎች መሰራት ኪራይ ሰብሳቢነትን በቀጥታ ባያስቀረውም፤ ቢያንስ የህዳሴውን ግድብ ያፋጥነዋል። በኔ እምነት… ሁሉም ነገር ግን መታየት ያለበት ከቀድሞው ባለራዕይ መሪ አቶ መለስ ዜናዊ ምልከታ አንጻር ነው። የዚህ ህንጻ ጠንሳሽ፤ የማይደፈረውን የደፈሩት አቶ መለስ ዜናዊ ናቸው። በመሆኑም ምስጋና የሚሰጥ ከሆነ፤ የሚጨበጨብም ከሆነ፤ ዘላለማዊ ክብር የምንሰጠው ለአቶ መለስ ዜናዊ ብቻ ነው።” ካሉ በኋላ፤ ካሉ



አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ - በእንቅልፍ ላይ።

በኋላ፤ “እኔ በግሌ ከሚቀጥለው ምርጫ በኋላ፤ በጠቅላይ ሚንስትርነት ላልቀጥል እችላለሁ። የተባለውንም ህንጻ ለማየት እድል አላገኝም ይሆናል። ስለዚህ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አልችልም።” በማለት ግራ የተጋባ መልስ ሰጥተው፤ በስፍራው የተገኙ ጋዜጠኞችን የበለጠ ግራ አጋብተዋቸዋል።

ይህን ዜና ከማጠቃለላችን በፊት ዜናውን በተለይ ለኢ.ኤም.ኤፍ በማቀበል የተባበረንን የህንጻው ዲዛይን አርክቴክቸር Loof LirpA ከልብ ለማመስገን እንወዳለን። በርግጥም የዚህ ቃል አቀባይ ስም ከኋላ ወደፊት ሲነበብ፤ April Fool ነው። እናም በየአመቱ አፕሪል 1ቀን ለምናከብረው፤ ለ2015 የሞኞች ጨዋታ ቀን አደረሳቹህ። ዘና ዜናችን እዚህ ላይ ያበቃል።